# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

**<u>ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የኢትዮ-ኤርትራን ድንበር በሚመለከት ከኢሕአዴግ መንግስት የቀረበውን "አዲስ ባለአምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብ" በመቃወም የተሰጠ መግለጫ::</u>**

ከሁለት ዓመት ማቅማማት በኋላ የኢሕአዴግ መንግስት የድንበር አካላይ ኮሚሽን የወሰነውን ውሳኔ "በመርህ" ደረጃ እንደተቀበለው ሰሞኑን ይፋ አድርጓል:: የኢሕአዴግ መንግስት በአሁኑ ወቅት ከዚህ አቋም ላይ ሊደርስ የቻለበት ምክንያት በውጭ መንግስታት የሚደርሰውን ተጽዕኖና ግፊት ለመቀነስና በተለይ በምርጫ ወቅት የውጭ ኃይሎችን እምነት አግኝቶ የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ የወጠነው ስልት መሆኑ ግልጽ ነው::

የኢሕአዴግ መንግስት ይፋ ያደረገው "አዲስ ባለአምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብ" የኢትዮ-ኤርትራን የድንበር ውዝግብ ይበልጥ ውስብስብና አስቸጋሪ ያደርገው እንደሆን እንጂ ችግሮችን አስወግዶ በአካባቢው ዘላቂ ሰላም ለማምጣት አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል ግምት የለንም::

እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ በመሣሪያ ኃይል ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የሕዝብን ተሳትፎና ውሳኔ ወደ ጐን አድርጐ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን ጥቅሞች የሚጻረሩ እርምጃዎች በተግባር ሲያውል መቆየቱ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያንና የአገራችንን ሁኔታ በቅርብ ሆነው ለሚከታተሉት ሁሉ ግልጽ ነው::

አሁን ላለው ችግር መነሻ የሆነው ለረዥም ዘመናት የወንድማማቾችን ደም ሲያፋስስ የነበረውና በሻዕቢያ ሲቀነቀን የነበረው የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመክርበትና ሀሳቡን ሳይሰጥበት፣ በኢሕአዴግና በሻዕቢያ መመሳጠር በሪፌሬንደም ስም የተፈፀመው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተውኔት (ደባ) ነው::


**ዋና መስሪያ ቤት** (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ. 18733 አዲስ አበባ ÷ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
**ስልክ ቁጥር** (Tel.No) 251-1530945 **ፋክስ** (Fax)

**ሰሜን አሜሪካ** (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

www.UEDF.com
e-mail Unitededf@yahoo.com

ይኸም እርምጃ ኢትዮጵያን ያለ ባህር በር ያስቀረ፣ በአካባቢ የሚኖሩ ብሔረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የተጻረረ፣ የአገሪቱን ዘለቄታዊ ብሔራዊ ጥቅም ፈጽሞ ያላገናዘበ፣ ወዘተ.... እንደነበር ምን ጊዜም የማይረሳ ጉዳይ ነው፡፡

የኢሕአዴግ ፀረ-ብሔራዊ ጥቅም ፖሊሲ የወለደውና በሻዕቢያ መንግስት ተንኳሽነት በተጫረው እሳትና ከዚህ ተከትሎ በመጣው የባድመ ወረራ ምክንያት በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሕይወታቸውን የገበሩበትና አካለ ስንኩል የሆኑበት፣ በብዙ ቢሊዮን የሚገመት ገንዘብ የወደመበት፣ ዜጎች ቤት ንብረታቸውን ጥለው የተሰደዱበትና የተፈናቀሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

አስከፊና ትርጉም የሌለውን ጦርነት አቁሞ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ተገቢ ቢሆንም ከሕግና ከዲፕሎማሲ አንጻር ተቀባይነት የሌለውንና የኢትዮጵያን ጥቅሞች አሳልፎ የሚሰጠውን የአልጀርስ "ስምምነት" የኢሕአዴግ መንግስት በጥድፊያ መፈራረሙን በቁጭት የምናስታውሰው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ የተጣደፈ፣ አስገራሚና ሕገ ወጥ ስምምነት መሰረት ጉዳዩን ምርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ የተደረገውና በወሰን አካላይ ኮሚሽንነት የተሰየመው አካል፤ ሕጋዊነት በሌላቸው የ1990፣ 1992 እና 1908 (እ.ኤ.አ) የቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት ድንበር እንዲካለል መፍቀዱና የኮሚሽኑም ውሳኔ ይግባኝ የማይኖረው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሆን ስምምነት ላይ መድረሱ፤ የኢሕአዴግ የአገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ የጣለ ደንታ-ቢስ የክህደት እርምጃ ነበር፡፡

የኢሕአዴግ መንግስት የአልጀርሱን ስምምነት ሲፈራረም፣ በሁሉም ረገድ ከፍተኛ መስዕዋትነት የከፈለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲወያይበት፣ ሃሳብ እንዲሰጥበትና እንዲወስንበት አላደረገም፡፡ በአባላቱና በደጋፊዎቹ የተሞላውን የይስሙላ ፓርላማ (ምክር ቤት) እንኳን በአግባቡ አላማከረም፡፡

ይህንን በአገዛዙ የተወሰደውን ሃላፊነት የጎደለው "ስምምነት" እና ብያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ከመነሻው አጥብቆ በመቃወም በየአደባባዩ የተቃውሞ ድምፁን አሰምቷል፤ አቤቱታውንም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ አቅርቧል፡፡

ይሁንናም ይህ የሕዝብ ተቃውሞ ሙግት ያጋጠመው ከአስመራ መንግስት በበለጠ በአቶ መለስ ከሚመራው የኢሕአዴግ መንግስት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጩኸቱና አቤቱታውም የሚገባውን ያህል ሰሚ ጆሮ እንዳያገኝ የኢሕአዴግ መንግስት ከፍተኛ ዴፕሎማሲያዊ ዘመቻ አካሂዷል፡፡

እንደተፈራውና እንደተጠበቀው የወሰን አካላይ ኮሚሽኑ የኢትዮጵያን ሕዝብና የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚጻረር፣ ህልውናዋን የሚፈታተን፣ ሕጋዊና ፍትሐዊ ያልሆነ ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ተቃውሞውን አልተወም፡፡

የኢሕአዴግ መንግስት በአልጀርስ ላይ ባደረገው ይግባኝ-የለሽ ስምምነት መሠረት የተሰጠውን ብያኔ ለመቀበል ያቅማማውና እስካሁን ተግባራዊ ለማድረግ የተቸገረበት ምክንያት ባጋጠመው ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ መሆኑ ግልጽ ነው::

ይህ የሕዝብ ተቃውሞ የረገበለት የመሠለው የኢሕአዴግ መንግስት ሰሞኑን ባለ አምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብ በማቅረብ የወሰን አካላይ ኮሚሽኑን ውሳኔ በመርህ ደረጃ የተቀበለ መሆኑን ገልጿል:: ለይስሙላ ያህልም ይህ አቋም ለፓርላማው (ምክር ቤት) ቀርቦ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ሙሉ ለሙሉ ሲቃወሙት 90 እጅ ከሙቶ በላይ የኢሕአዴግ በሆኑት የፓርላማ አባላቱ ፀድቋል ተብሏል::

የኢሕአዴግ መንግስት የኮሚሽኑን ውሳኔ "በመርህ" ደረጃ የተቀበለው በውጭ መንግስታት ግፊት ምክንያት መሆኑን ሳይደብቅ ከመግለጹ በተጨማሪ የውሳኔው ተግባራዊነት ድርድር ለማካሄድ እንዲያስችለው መሆኑን ገልጿል:: በድንበር ጉዳይ ላይ ድርድር ለማካሄድና በአካባቢው ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ከተፈለገ በተለያዩ ጉዳዮች ተወያይቶ ስምምነት ላይ ለመድረስ የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚያስከብሩ፤ ነገር ግን በአልጀርሱ ስምምነት አሳልፎ የተሰጡ የተለያዩ መሰረታዊ ጉዳዮች መነሳትና ስምምነት ላይ መድረስ እንጂ ቀደም ብለው በተቀበሉት ውሳኔ ላይ ተመስርቶ መደራደር አይደለም:: በውይይትና በድርድር የተፈጠሩትን ችግሮች መፍታት የሚለው መሠረተ ሃሳብ የአልጀርሱ ስምምነት አካል ቢሆን ኖሮ በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው ችግር ሊፈጠር አይችልም ነበር::

ችግሩን በሰላማዊ መንገድ በድርድርና በውይይት መፍታት የሚደገፍ ቢሆንም የኮሚሽኑን ውሳኔ በመርህ ደረጃ እየተቀበለ ተግባራዊነቱን እንዴት መቃወም እንደሚቻል ግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልተገለጸም:: ያለ ይግባኝ እቀበለዋለሁ የተባለን ውሳኔ ተግባራዊነቱን እቃወመዋለሁ ማለት ሕገ ወጥ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ተጻራሪው ወገን "ፍርዱ ተግባራዊ ይደረግ" በሚለው አቋም ከገፋ ውሳኔውን የሚሽር ምን ዓይነት የሕግ ማስተማመኛ ሊኖር እንደሚችልም ግልጽ አይደለም:: የኢሕአዴግ መንግስት የኮሚሽኑን ውሳኔ "በመርህ ደረጃ ተቀብለን " ተግባራዊነቱ ላይ ግን እንደራደራለን በሚል አስተሳሰብ ያቀረበው ሃሳብ፤ የኮሚሽኑን ውሳኔ ያለ ይግባኝ እቀበለዋለሁ ያለውን የመጀመሪያ አቋሙንና በኋላም በሕዝብ ተቃውሞና ግፊት ውሳኔው ሕገ-ወጥና ኢ-ፍትሐዊ ነው በማለትና በመቃወም የወሰደውን አቋም በተምታታ መልክ ለማስታረቅ የተጠቀመበት ስልት መሆኑ ግን ግልጽ ነው::

በኢዴፓኅ እምነት መወሰድ ያለበት እርምጃ ችግሮቹ ለመስዕዋት ከፋዩና ለባጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እየሆኑ፣ አማራጭ በሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦች ላይ ሕዝቡ በቀጥታም ሆነ በተወካዮቹ አማካይነት ሃሳብ እንዲሰጥ እየተደረገ ድርድሩን በማካሄድ ፍትሐዊና ዘላቂ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሔዎችን ማስገኘት መቻል ነው::

አሁን በጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ የሚቀነቀነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቀበል በላዩ ላይ ለመጫን የሚደረገው የሰላም ሃሳብ ቀደም ሲል ሊታሰብበት በተገባ ነበር::

ነገር ግን የኢሕአዴግ መንግስት ምንም ሕጋዊነት በሌለው መሠረት ላይ ያረፈን ውል፣ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ አካሄድ ገለልተኛነቱ ባልተረጋገጠበት አካል የሚሰጥን ይግባኝ የለሽ ብያኔ ለመቀበል ከሕዝብ ጀርባ አስቀድሞ መስማማትና ይባስ ብሎም ከጠላት በባሰና በጠነከረ ሁኔታ የሕዝብን ተቃውሞ በየአደባባዩ ሽንጡን ገትሮ ሲሞግት ቆይቷል:: ይህ አካሄድ ውሎ አድሮ አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚያስገባ አለማወቅ፣ ወይም የሚወስዱት እርምጃ የሚያስከትለውን ጉዳት ለማገናዘብ የያለመፈለግ ደንታ-ቢስነትና የናጠጠ የሕዝብ ንቀት ወይም የሁለቱም ድምር ከመሆን አያልፍም:: ስለሆነም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የሚደረግ ማንኛውም ድርድርና ውል በተግባር ለማዋል ሲፈለግ ውሎ አድሮ ገሃድ መውጣቱና ሴራውም በአደባባይ እንደሚጋለጥ አለማመዛዘን "ግመል ሰርቆ አጎንብሶ" ዓይነት መሆኑን ኢሕአዴግ የተገነዘበው አይመስልም::

በጠመንጃ ኃይል ስልጣን ይዞ፤ ከዚያም በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣኑን እንዳረጋገጠ የሚሰማው ኢሕአዴግ ባለፉት አስራ አራት ዓመታት የስልጣን ዕድሜው በርካታ ሕዝብንና አገርን ጉዳት ላይ የጣሉ ፖሊሲዎችን ያወጣ፣ የተከተለና በስራ ላይ ሲያውል የነበረ መንግስት በመሆኑ አሁንም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በሚያስከብርና ብሔራዊ ጥቅሟን በሚያረጋግጥ፣ የሕዝብን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ ተደራድሮ መፍትሔ ያስገኛል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው:: ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአንዱ ቀውስ ወደ የባሰ ቀውስ ሲያሸጋግረን የነበረው የኢሕአዴግ አመራር ይህን ችግር ከማባባስና አዳዲስ ችግሮችን ከመቀፍቀፍ አልፎ ዘላቂ መፍትሔ ሊያስገኝ የሚችል ብቃት እንደሌለው የተጓዘበት ታሪኩ ይመሰክራል::

ስለሆነም ለኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጉዳይ ትክክለኛ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው የሕዝብን መብት ገድቦ እንዳሻውና በሚፈለገው መልክ እየወሰነ ተግባራዊ ከሚያደርገው ከኢሕአዴግ መንግስት ሳይሆን እውነተኛ የሕዝብ ወኪል ከሆነና በሕዝብ ከሚመረጥ መንግስት ብቻ ነው:: ለዚህም ሆነ ለሌሎች ችግሮቻችን መፍትሔ ለማግኘት የመጀመሪያው እርምጃ ነፃና ፍተሐዊ ምርጫ በአገራችን እውን እንዲሆን በህብረት በመታገል በስልጣን ላይ ያለውን የኢሕአዴግ አምባገነን መንግስት ማስወገድና በምትኩ ሕዝባዊ መንግስት ማቋቋም ነው::

ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን ባሟላ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሚሰየመው መንግስት እውነተኛ የሕዝብ ወኪሎች የሚገኙበትን ምክር ቤት እያማከረ፣ ሕዝብን እያሣተፈና ውሳኔ እንዲሰጥበት እያደረገ በአሁኑ ወቅት ለተፈጠረው ችግር ተገቢና ዘላቂ መፍትሔ ይፈልጋል::

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ማናቸውም ሀገራችን የምትቀበለው ዓለም አቀፍ ስምምነትና ውል በውጭ ኃይሎች ጫና የሚከናወን ሳይሆን የአገራችን ብሔራዊ ክብርና ሉዓላዊነቷ በተከበረበት ሁኔታ የሕዝቧ ሰላምና ጥቅም ተከብሮ የአካባቢውን ሰላምና መረጋጋት በሚያሰፍን መልክ እንዲሆን፣ ከባለ ጉዳዩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እየመከረ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት ሲገልጽ፣

ፀረ-አገር፣ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሰላም እርምጃዎችንና የኢትዮጵያን ጥቅሞች ለሌላ ወገን አሳልፎ የሚሰጡ ስምምነቶችን በማውገዝ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በኢሕአዴግ በአገራዊና ብሔራዊ ጥቅሞቻችን ላይ የተቃጣውን ሴራ ለማክሸፍ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሙያና የሲቪክ ድርጅቶች፣ በየክፍለ-ዓለሙ ላሉ ኢትዮጵያዊያንና እንዲሁም ለሁሉም ሰላም ወዳድና አገር ወዳድ ወገን ዓለም-አቀፍ የተቀናበረ እንቅስቃሴ እንዲደረግ የጋራ ትግል ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**የተረጋገጠና አስተማማኝ ሰላም በሕዝብ ፍላጐት ይረጋገጣል!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና አገራዊ አንድነት በሕዝብ የተባበረ ትግል እውን ይሆናሉ!!**
**ድል በኅብረት!!!**

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ኅዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም
አዲስ አበባ፡፡